# መነሻችንን ብቻ ሳይሆን መድረሻችንንም እናውቃለን

ስሜነህ 12-21-16

መዋቅራዊ ለውጥ ያመጣል ተብሎ የሚጠበቀው ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ አንድ አመት ማስቆጠሩ ይታወቃል፡፡ በዚህ ሂደት ወይም በዕቅድ ዘመኑ የመጀመሪያ ዓመት ሃገሪቱ አጋጢሟት ከነበሩ አስቸጋሪ ፈተናዎች መካከል ከአየር ንብረት መዛባት ጋር ተያይዞ የተከሰተውን ድርቅ የሚተካከለው የሌለ መሆኑም እሙን ነው። ሃገራችን ይህንን የድርቅ አደጋ የተቋቋመችበት አቅምና አፈፃፀም ደግሞ ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መፈፀም የሚያስችል አቅም መገንባቷን አመላክቶን ያለፈ መሆኑም የማይተባበል እና አለም የመሰከረልን ሃቅ ነው ፡፡

በሃገራችን የሃምሳ ዓመታት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውና ሰፊ አካባቢ ያካለለውን የድርቅ አደጋ፣ ለዜጎች በየቀያቸው ዕርዳታ በወቅቱ በማቅረብ ምንም ዓይነት የህይወት አደጋ ሳያስከትል መቋቋም መቻሉ በሃገሪቱ የእየተገነባ ያለውን የአመራርና የአፈፃፀም ዕድገት በሚገባ አመላክቷል፡፡ በቀሪዎቹ ጊዜያት ይህንን አቅም ሙሉ በሙሉ በልማት ተግባር ላይ በማዋል ዕቅዱን የማሳካት ዕድል ሰፊ መሆኑንም አረጋግጧል፡፡

እስካሁንና በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተገነቡት መሰረተ ልማቶች፣ ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬታማነት ትልቅ አቅም መሆናቸው ሌላው ተፈፃሚነቱን ከወዲሁ የሚያመላክት እውነታ ነው፡፡ ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአገሪቱን የኢኮኖሚ አውታር በማስፋት፣ ኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ወሳኝ ሚና እንዲጫወት በማድረግና የወጪ ንግድን በማሳደግ፣ የአገሪቱን የህዳሴ ጉዞ ማሳለጥ በሚያስችለው ደረጃ ላይ ደርሷል ፡፡

ወጣቱ ትውልድ በገጠርና በከተማ ልማት በማሰማራት የስራ ዕድል ከመፍጠር ጎን ለጎን የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሃይል ለማድረግ የተያዘው ዕቅድ የገጠሩን አጠቃላይ ገፅታ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚለውጠው ይታመናል፡፡ የመስኖ ግብርና፣ የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንደዚሁም የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ስራ በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋትን ትኩረት ያደረገው ዕቅድ፣ ግብርናው በዕቅድ ዘመኑ ለልማቱና ለፈጣን ዕድገቱ የማይተካ አስተዋፅኦ ከማድረግ ባሻገር የዘመናዊ አምራች ዘርፍ ዕድገት ዋና ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል

እንደሚያስችለው ካመላከቱ ጉዳዮች መካከል ከሁሉም የሃገሪቱ አቅጣጫዎች ወሳኝ የሆኑትን እና በአስረጂነት ሊጠቀሱ የሚችሉትን አንስቶ ለበለጠ አፈጻጸም የሚያግዙትን ተሞክሮዎች ማንሳት የዚህ ተረክ አብይ ጉዳይ ነው፡፡

የመጀመሪያው አስረጃችን የሚወስደን ወደ ኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን ነው ። በባሌ ዞን ዘመናዊ መስኖ ልማትን ለማስፋፋት ከ80 ሚሊዮን ብር በሚበልጥ ወጪ እየተገነቡ የሚገኙትና በመጠናቀቅ ሂደት ላይ መሆናቸው ከሰሞኑ በይፋ የታዩት የ10 ዘመናዊ መስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ ስለሁለተኛው ዙር የግብርና እቅድ አፈጻጸም ሁነኛ ማሳያዎች ናቸው።

በየወረዳዎቹ ከሚገነቡት የመስኖ ፕሮጀክቶች መካከል አራቱ ዘንድሮ የተጀመሩ አዳዲስ ሲሆን ቀሪዎቹ ካለፈው ዓመት የተሸጋገሩ ናቸው፡፡ የነባር ፕሮጀክቶች ስራ ከ80 በመቶ በላይ ደርሷል። እነዚህ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አንድ ሺህ 435 ሄክታር በላይ መሬት በማልማት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ከማድረጋቸውም በላይ መድረሻ ግብ ለሆነው የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ግብአት የሚሆኑ ምርቶችን በማልማት ለገጠር ወጣቶች ሰፊ የስራ እድል የሚፈጥ መሆናቸው አለማጠያየቁ ነው በአስረጂነት እንድንጠቅሰው ያስቻለን፡፡ የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በበጀት ዓመቱ በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ለማብቃት ከወዲሁ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ሦስት ሺህ የሚጠጉ አርሶና ከፊል አርብቶ አደሮች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ከዞኑ ግብርና መምሪያ የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ። በባሌ ዞን በአሁኑ ወቅት በባህላዊና ዘመናዊ መስኖ እየለማ ያለውን ከ70ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ማብቂያ ላይ ወደ 163ሺህ ሄክታር ለማድረስ ግብ ተጥሎ እየተሰራ መሆኑም ተመልክቷል፡፡

አሁን ደግሞ ወደአማራ ክልል ሰሜን ወሎ አቅንተን ተጨማሪ አስረጅ እናምጣ። በሰሜን ወሎ ዞን በተያዘው የበጋ ወቅት ከ66ሺ ሄክታር በላይ መሬት በመስኖ ለማልማት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን የዞኑ ግብርና መምሪያ ያስታወቀው ባለፈው ወር ነው፡፡ የመስኖ ልማቱን ለማካሄድ የታቀደው ነባርና አዲስ የመስኖ አውታሮችን በመጠቀም ነው።

ይህ እንቅስቃሴ አጠቃላይ በተያዘው የሁለተኛው ዙር የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን የሚከናወን ሳይሆን በዚህ አመት እና ይህም በአንድ ዞን ብቻ የሚፈጸም መሆኑ በእቅድ ዘመኑ ማብቂያ ከላይ በተመለከተው አግባብ የት እንደምንደርስ በማያወላዳ መልኩ የሚያመላክት ነው።ነገርዬውን እስኪ ዘርዘር እናድርገው። በዚህ አመት ሊያውም በበጋ ወቅት ብቻ ከ292ሺ በላይ አርሶ አደሮችን በማሳተፍ 66ሺ 200 ሄክታር የሚጠጋ መሬት በማልማት ከ7 ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ዞኑ ግብ ጥሎ እየተጋ ሲሆን በትጋቱ ልክ ውጤት የሚያስመዘግብ አቅም ላይ መድረሱን አመላካች የሆኑ ፍሬዎች አፍርቷል።

እስካሁን በተካሄደ እንቅስቃሴ ቀድሞ የደረሰ ሰብልን ፈጥኖ በመሰብሰብ 16 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት በመስኖ መልማቱ አንደኛው እና አመርቂ ለሚሆነው አፈጻጸም አመላካች የሚሆነው ፍሬ ነው፡፡ ከማሳ ዝግጅት ጎን ለጎንም ሽንኩርት፣ በርበሬ፣ ቲማቲምና ቀይ ስር የመሳሰሉ ችግኞችን ቀድሞ የማፍላት ስራ መሰራቱም በተመሳሳይ፡፡

ዘንድሮ በመስኖ የሚለማው መሬት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ12ሺ ሄክታር መሬት ብልጫ ያለው መሆኑ ደግሞ የአፈጻጸሙን አመርቂነት የበለጠ እና በግልጽ የሚያመላክት ነው፡፡

ይህ ዞን ዝናብ አጠርና በተደጋጋሚ ድርቅ የሚያጠቃ መሆኑ ቢታወቅም ያለውን በቂ የከርሰና የገጸ ምድር ውሀ ሃብት በመጠቀም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንዲቻል በመስኖ ልማት ለሚሳተፉ 159 ሺህ አርሶአደሮች በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አዳዲስ አሰራሮችን የመተግበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መሰራቱም የአፈጻጸሙን አመርቂነት ከጥርጣሬ የሚያነጻ ነው።

በመስኖ ልማቱ ምርታማነትን ለማሳደግም 504 ኩንታል ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ሲሆን፤ ለመስኖ ልማት የሚውል 397ሺ 831 ሜትር ኪዩብ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በአርሶ አደሩ መዘጋጀቱና፤ የመስኖ ልማቱን አጠናክሮ ለመቀጠልም አርሶ አደሩ በአሁኑ ወቅት በደለል የተዘጉ ቦዮችን በዘመቻ በመጥረግ ለልማቱ አዘጋጅቶ መጨረሱ የጸረ ድህነት ዘመቻውን በድል መጠናቀቅ ከወዲሁ የሚያበስር ነው፡፡

በሰሜን ወሎ ዞን ባለፈው ዓመት የነበረውን ድርቅ በመቋቋም በመስኖ ከለማው ከ54ሺ ሄክታር በላይ መሬት ከ4 ነጥብ 1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማምረት መቻሉን ከዞኑ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

የሁለተኛው ዙር እቅድ ዘመን ከተጀመረበት ማግስት ጀምሮ በመላው ሃገራችን የሚገኙ አርሶአደሮች በየጓሯቸው የሚገኙ ቅጠላ ቅጠሎችን እና ተረፈ ምርቶችን እንዲሁም ሌሎች በየአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማዘጋጀት ምርትና ምርታማነታቸውን እጽፍ ድርብ ማድረስ መቻላቸው ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋም ካስቻሉና የአርሶአደሩን ተነሳሽነት በከፍተኛ ደረጃ ካሳደጉ ምክንያቶች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀም ከጀመሩ ወዲህ የማሳቸው ለምነት በመጨመር የሚያገኙት ምርትም እየተሻሻለ መምጣቱን በሁሉም አቅጣጫዎች የሚገኙ አርሶአደሮች እየመሰከሩ ነው፡፡ ቀደም ሲል ከአንድ ሄክታር መሬት ላይ ያገኙት የነበረውን ከ30 ኩንታል ያልበለጠ ምርት የተፈጥሮ ማዳበሪያ /ኮምፖስት/ መጠቀም ከጀመሩ ወዲህ ወደ 41 ኩንታል ለማድረስ ያስቻላቸው እንደሆነም የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚንስቴርን እና በየወረዳው የሚገኙ የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ጽህፈት ቤቶችን ዋቢ ያደረጉ መረጃዎች አመልክተዋል።

የተፈጥሮ ማዳበሪያው ምርታማነትን ከመጨመር ባለፈ ባለፉት ሁለት ዓመታት ለፋብሪካ ማዳበሪያ ግዢ ያወጡት የነበረውን ከ3ሺ 800 ብር በላይ ወጪ በማዳን ለሌሎች የልማት ስራዎች ማዋል እንዲችሉም ምቹ አጋጣሚን ፈጥሯል። የተፈጥሮ ማዳበሪያ የመሬትን ለምነትን ከመጨመር ባለፈ ወጪን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው በተግባር መታየቱ ደግሞ ከሌሎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና ምርጥ ዘሮች ጋር ተደምሮ ድርቅን ከመቋቋም ባለፈ አጠቃላይ በሆነው ግብርናችን ላይ የሚያመጣውን መዋቅራዊ ለውጥ መገመት አይከብድም።

በዚህና መሰል በሆኑ የግብና እንቅስቃሴዎች የሚገኙ ውጤቶችን መነሻ በማድረግ የገጠር ወጣቶችን በግብርና ማቀነባበሪያው ዘርፍ በስፋት ማሳተፍ ከተቻለ በእቅድ ዘመኑ ሃገሪቱ

የጣለችው አጠቃላይ የልማት ግብ መነሻና መድረሻውም ይኸው ስለሆነ የሃገሪቱ ህዳሴ በማይነቃነቅ አለት ላይ መሰረቱን የሚጥል ይሆናል፡፡

ይህ የማይናወጥ መሰረት ላይ የተጣለ የህዳሴ ጉዞ የገጠር ኢንዱስትሪ ማዕከላት በሂደት እየተፈጠሩ ከተሞቻችንም በዛው መጠን እንዲያድጉ በማስቻል የህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ እየተቀየረ፣ የከተማና የገጠር ትስስር እየጠበቀ፣ ያደገ ህብረተሰብ ለመገንባት የሚያስችለን አቅም የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳያ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬታማ ይሆን ዘንድ የገዢውን ፓርቲ ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚ ፓርቲዎችን፣ የሲቪክ ማህበራትን፣ በየደረጃው የሚገኙ  የመንግስትና የህዝብ የልማት አቅሞችን አደራጅቶ በብቃት መምራት የሃገሪቱን እጣ ፈንታ ከሚወስኑ ቁልፍ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ይሆናል፡፡